EthioLion

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

የካቲት 12 2002

## ይድረስ ለኢትዮጵያ ወጣቶች

በጫንቃችሁ ላይ የተቆናጠጠው የመለስ አገዛዝ ነጻ፤ ፍትሃዊ፡ ሰላማዊ፡ እውነተኛና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ለማካሄድ የሚያስፈልጉትንና በኢሕአፓና በሌሎች ሀገር ወዳዱ ኃይላት የቀረቡለትን ቅድመ ሁኔታዎች ወደጎን በማድረግ ራሱ ብቻ በአሸናፊነት ሊወጣ የሚችልበትን ስልቶችን ቀይሶ፤ መሰናዶውን አጠናቆ ባለበት ሁኔታ እናንተንና ሕዝብን የምርጫው ተውኔት ተካፋይና ታዛቢ ለማድረግ እየጣረ መሆኑን ትመለከታላችሁ። ለዚህም ደግሞ ከፍተኛ የሕዝብ ሀብት በማባከን መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ መሆኑንም የምትገነዘቡት ነው። ሕዝብ ደግሞ በተለያየ መልክ ቀልዳችሁን ማየት አልፈልግም እያላቸው መሆኑንም የምትረዱለት ጉዳይ ነው። መብቶቻችሁን ገድቦ፤ የሀገር ባለቤትነታችሁን ረግጦ፤ ነፃነታችሁን ገፎ እንዳሻው እየፈነጨ፤ በተለያዩ ጊዜያዊ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለልና ሳይቻለው ሲቀር በማስገደድ፣ የድርጅቱ አባል እያደረጋችሁ የቀልዱ ተካፋይ ሊያደርጋችሁ መንቀሳቀሱ መሰሪነቱንና፡ በንቀትና በትዕቢት የተወጠረ መሆኑን በቀን ተቀን ኑሯችሁ የምታውቁት ነው። ይህንን እብሪቱን ማስተንፈስ የዜግነት ግዴታ ነው ብንል ሃቁን መናገር ነው።

በኑሮ ውድነት መሰቃየታችሁ፡ የወደፊቷ ኢትዮጵያ አለኝታ እንድትሆኑ በሚያስችላችሁ ትምህርት እንዳትታነጹ መደረጋችሁ፡ የትምህርት ዕድል ያገኛችሁትም ተምራችሁ ለሥራ አጥነት መዳረጋችሁ፡ በጤና ጉድለት፤ በአልባሌና ሰብዓዊ ክብር-ነክ በሆኑ ተግባራት ለመሰማራት መገደዳችሁ፡ ኑሯችሁን የሚያሳይ መራር ዕውነታ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት አድርጋችሁ የወደፊት እጣችሁን በራሳችሁ እንዳትወስኑ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክና ባሕል ተረድታችሁ በመጠበቅና በመንከባከብ፡ ከረሃብና ከችግር ተላቃችሁ በእድገትና ልማት ጎዳና እንዳትጓዙ ለማድረግ በአሁኑ ወቅት በየአራት አመቱ በሚደረግ የምርጫ ተውኔት እንድትወጠሩ እያደረገ መሆኑን የምታጡት አይደለም። አገዛዙ በሚከተለው ፖሊሲ የተነሳ በሀገሪቱ የሰፈነው ረሃብ፡ የድርቅ መስፋፋት፡ ንፅህናው የተጠበቀ የውሃ አቅርቦት ዝቅተኛነት፤ በቂ የጤና አገልግሎት አለማግኘት፡ በሥርአተ ጾታ እኩልነት ዙሪያ ያለው አሳዛኝና አሳፋሪ ሁኔታ፡ (የኤድስ፤ የወባና ሌሎች የወረርሽኝ በሽታዎች እዚህ ላይ ታክለው) እንዲሁም ተፈጥሮን በተገቢው መንገድ አለመንከባከብ በናንተ ላይ እያደረሱ ያሉ መጠነ ሰፊ ጉዳቶች በቀላሉ የሚገመቱ እንዳልሆኑም የምታውቁት ነው።

የወላጆቻችሁ ሸክም ላለመሆን የምታደርጉትን ጥረት እያኮላሸ መሆኑን ከናንተ በላይ የሚረዳ ሊኖር አይችልም። ራሱ የማያከብረውን በሕዝብ ይሁንታ ያላገኘውን ሕገ አገዛዙን አክብራችሁ እንድታስከብሩ፡

Ethiopia will prevail !

የሁከትና የአለመረጋጋት ምክንያት ራሱ ሆኖ ሳለ ተቃውሞ በማሰማታችሁ ደንግጦ በአመጽ አትሞክሩኝ እያለ ይደነፋባችኋል። የትግል አንድነት እንዳትፈጥሩበት በጸጥታው፤ በፖሊሱና በወታደራዊ ተቋማቱ ውስጥ እያስገባ እርስ በርስ ያናክሳችኋል። ወላጆቿችሁን፤ ዘመዶቻችሁን ብሎም ባጠቃላይ ዜጎች ወንድምና እህቶቻችሁን በሱ ስምና አዛዥነት እንድትጨቁኑ፤ እንድትገድሉ፤ እንድታስሩ እየሸረበ በሰላይነትም እያሰማራ ከሕዝቡ ጋር ያላችሁ ግንኙነት እንዲበጠስ እያደረገ በተወለዳችሁበት በቀዬቻሁ ባደጋችሁበት አካባቢ በባይተዋርነት እንድትኖሩ እየቀመረባችሁ ይገኛል። በየጊዜው እየከዱት ያሉት ባለሥልጣናቱ የሰጡት የምስክር ቃል የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ነው። ይህንን አዙሪት ሰብሮ እንዳለፉት የዛ ትውልድ አባላት አኩሪ የጀግንነት ታሪክ አስመዝግባችሁ፤ ሁሉም ዜጋ በሀገሩ በነጻና በሰላም የሚኖርባት ኢትዮጵያ እንድትገነባ የናንተ የበኩላችሁ አስተዋጽዖ ከፍተኛ መሆኑን በሚገባ የምትረዱት ነው። ለዚህ ወቅቱም አሁንና በጣምም የተመቻቸ ነው።

በመልካም አርዓያነትና በትግል ኃዋሪያነት ልትመለከቷቸው የምትችሉት የዛ ትውልድ አባላትና ተከታዮቻቸው በጠቅላላ በሀገሪቱ አሉላችሁና ታሪካቸውን ከወላጆቻችሁ ከዘመዶቻችሁ ጠይቆ መረዳቱ ይበልጥ ጠቃሚ ነው። ተደራጅታችሁ ከፈለጋችኋቸው ደግሞ መገናኘቱ የሚከብድ አይሆንም። ከብሔራዊ ጥቅም ይልቅ በግል ሃሳብና በውሸት ብቻ የተመረኮዙ፤ በሚያማምሩና በሚያነኾልሉ ቃላት የተሞሉና ምንም ተጨባጭነት የሌላቸው የወያኔ ፕሮፓጋንዳን ከሚመስሏችሁ ጋር በመወያየት ለህዝብ ማጋለጥ ከናንተ ከምንጊዜውም በላይ የሚጠበቅ ግዳጃችሁ መሆኑንም የምታውቁት ነው።

የነገዪቱ ኢትዮጵያ አመራር ተረካቢና መጻኢ እድሏንም ወሳኝ ናችሁና ይህንን ሕዝብን የሚያኮራ ኃላፊነት ለመሸከም አዕምሮዓዊ ብቃታችሁን የምታስመሰክሩበት ወቅቱ አሁን በመሆኑ ኢሕአፓ የትግል ጥሪውን ያደርግላችኋል። በሀገራችን ለተከሰቱት ችግሮች ሁሉ በዋናነት ተጠያቂው የመለስ አገዛዝ ነውና ለዚህም በጎሳና በሃይማኖት ከመከፋፈል አንስቶ የተለያዩ ጋሬጣዎች እየደቀነ የሚያንገላታችሁ ብቻ በቂ ምስክር ነውና የትግል ትኩረታችሁ በሱ ላይ መሆን አለበት። እውነተኛና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ እንዳይኖር እንቅፋቱ አገዛዙ ሆኖ ሳለ የሱ እኩይ ተግባር አባሪና ተባባሪ እንድትሆኑለት የሚያደርገውን ጥረት ማክሸፍ የወቅቱ ዋና ተልዕኳችሁ ሊሆን ይገባል። ሀገርን፣ ሕዝብን፣ ወላጅ ዘመድንም የሚያኮራም ተግባር ነው።

የሀገርን ጥቅም የመጉዳት ጥፋቶች በአፄውም፡ በደርግም የተካሄደ ነውና ወያኔ ለብቻው ተነጥሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት አያሰኘውም እያሉ የመለስ አገዛዝን እውነተኛ ጠባይና የሕዝብ ጠላትነቱን ለመሸፈንና ለማድበስበስ የሚከጅላቸውን ወያኔዎችና ተለጣፊዎችን አጥብቆ መታገል ታግሎም ከሥልጣን ማስወገድ ጊዜው አሁን ነው። ሀገርንና ሕዝብን በስልት ይሁነኝ ብሎ ለመከፋፈል፡ ለማስገንጠል በኋላም እንደታየው



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ለታሪካዊ ጠላቶቿ ለም መሬቷን ለመቸበቸብ የመጣ ዋና ጠላቷ መሆኑን ተገንዝባችሁ፤ ለወያኔ ተንኮል ሰለባ ከመሆን ይልቅ የምርጫ ተአቅቦ መፈከር አንግባችሁ ወላጅ ዘመዶቻችሁን ጓደኞቻችሁን መቀስቀስና ወያኔን እርቃኑን ማስቀረት ይጠበቅባችኋል። „የማይናቅ ሥራ ተሰርቷል ፍሬያማ ውጤት ተገኝቷል ይህ ማለት ግን ችግር የለም አጥጋቢ ነው ማለት አይደለም“ እያሉ በትናንሽ ስኬት መላ ገመናቸውን ለመሸፈን የሚያደርጉት ፕሮፓጋንዳ የዴሞክራሲ ካባ ሊያላብሳቸው እንደማይችል በዕለት ተዕለት ኑሯችሁ በሚገባ የምትረዱት ነውና ይህንን ድርጊቱን በምርጫው ተአቅቦ መፈክር እያጀባችሁ የወቅቱም ዋና ተልዕኮ ይኸው ብቻ መሆኑን ተገንዝባችሁ እንድትታግሉ ኢሕአፓ ይህንን ጥሪ ያቀርብላችኋል። ድርጅታዊና ፖለቲካዊ ጥንካሬና ጉልበትን ፈጥሮ የመለስ አገዛዝ የማያሽሟጥጥበትን ተፅዕኖ ለማሳረፍ እስካልተጣረ ድረስ የአቅመ ቢስ ልመናና በወያኔ ምርጫ መሳተፍ የትም እንደማያደርስ እያስገነዘቡ መታገል፡ እየታገሉ መሰባሰብ፡ እየተሰባሰቡ መጠናከርና እየተጠናከሩም ለድል መታገል ወሳኝም አስፈላጊም ነውና ተደራጁ ሕዝብንም አደራጁ። ወጣቱን ለማደራጀት የኢህአፓ ወጣት ክንፍ (ወክንድ) ተመስርቷልና በእሱም ስር ተደራጁ፣ ተሰባሰቡ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነቱን ለማስጠበቅ የቻለው በራሱ የጸና ትግል እንጂ በባዕዳን ነጻ አውጪነት እንዳልሆነ የቀድሞ አባቶቻችሁ፤ እናቶቻችሁና አያቶቻችሁ አሳይተዋል። ኢትዮጵያን በትግላቸው የተረከብናት ኢትዮጵያ አድርገው በደማቸውና በአጥንታቸው አኩሪ ታሪክ ሰርተው ለተተኪው ትውልድ አስተላልፈዋል። መብትን ማስከበርና ዴሞክራሲን የመገንባቱ ጉዳይም ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደጋፊም አድናቂም የሚያገኘው በራሱ የጸና ትግል ብቻ ነው። ይህችን በርካታና አኩሪ የታሪክ ምዕራፍ ያላት ሀገራችሁን በሌላ በትግል በደም ቀለማችሁ በምትጽፉት ታሪክ ከወያኔ መንጋጋ ማላቀቅና አዲስ የታሪክ ሂደት ጎዳናን ለመክፈት ታጥቃችሁ መነሳት አማራጭ የለውም። ኢትዮጵያ የናንተ የልጆቿ እንጂ የሌላ ከቶ ልትሆን አትችልም። በዚህ ጽኑ የትግል ሂደት ደግሞ ኢሕአፓ ምንጊዜም ከጎናችሁ ነው።

በተባበረ ትግል እናቸንፋለን!!
የኢትዮጵያ ወጣት የሕዝቡ አለኝታ ነው!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

EthioLion.com